# ግንቦት ሰባትም የግንቦት 20 ድል ውጤት ነው!

ኢብሳ ነመራ 05-27-17

የኢትዮጵያ የመንግስት ታሪክ የአንድ ከሩብ ክፍለ ዘመን ያህል እድሜ አስቆጥሯል። በዚህች ምድር ከዚያ ቀደም መንግስት አልነበረም እያልኩ እንዳልሆነ ልብ በሉ። በሰሜን ኢትዮጵያ ሶስት ሚሌኒየም ያህል እድሜ ያስቆጠረ የመንግስት ታሪክ ነበረ። የደቡብ፣ ምስራቅና ምእራብ ኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችም እንዲሁ ክፍለ ዘመናትን ያስቆጠሩ የየራሳቸው የመንግስት (የአስተዳደር) ስርአቶች ነበራቸው።

አንድ ከሩብ ክፍለ ዘመን እድሜ ባስቆጠረው የኢትዮጵያ የመንግስት ታሪክ ውስጥ ሶስት ስርአቶች ተፈራርቀዋል። እነዚህም በፊላጭ ቆራጭ ነገስታት የሚመራ ዘውዳዊ ስርአት፣ የወታደራዊ የቡድን ፈላጭ ቆራጭ ስርአትና አሁን ያለው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) የመንግስት ስርአቶች ናቸው። በዚህ ጽሁፍ በሶስቱ ስርአቶች የህዝብን የበላይነት ከማረጋገጥ አኳያ የነበረውን ሁኔታ በንጽጽር ለመዳሰስ እሞክራለሁ። በቅድሚያ ግን ስለሃገርና የህዝብ የበላይነት እንዲሁም ስለመንግስት የስልጣን ምንጭ አጭር ነገር ማንሳት እፈልጋለሁ።

ሃገር ግኡዝ በወሰን የተከለለ መሬት አይደለም። ሃገር ወንዝ፣ ሃይቅ፣ ተራራ፣ ሸንተረርና ሸለቆም አይደለም። ሃገር በአንድ የተወሰነ መልከዓ ምድራዊ ወሰን ውስጥ የሚኖር መስተጋብር ያለው ህዝብ ነው፤ ሃገር ግዙፍ ማህበረሰብ ነው። ህዝቡ የሚኖርበት መሬትም የህዝቡ ነው። ሃገር ህዝብ ከሆነ ያንን ህዝብ የሚያስተዳደር መንግስት ከህዝቡ ውጭ ከየትም ሊመጣ አይችልም። ይህ የህዝብ የበላይነት መርህ ነው። በመርህ ደረጃ የመንግስት ስልጣን የሚመነጨው ከህዝብ ብቻ መሆን ይኖርበታል። ከህዝብ ውጭ የተገኘ ስልጣን፣ መነሻው መለኮታዊም ይባል፣ ርዕዮተዓለማዊ በመርህ ደረጃ ተገቢ አይደለም።

ወደኢትዮጵያ የመንግስት ስርአቶች ስንመለስ፣ በየራሳቸው ስርአት ሲተዳደሩ የኖሩ ብሄሮችንና ብሄረሰቦችን በተስፋፊኒት ተቆጣጥሮ በአሃዳዊ ስርአት ሲያስተዳድር የነበረው አሃዳዊ የነገስታት ፈላጭ ቆራጭ ስርአት የስልጣን ምንጩ መለኮታዊ እንደነበረ በይፋ አውጆ ነበር። የመግዛት ስልጣኑ ከህዝብ ፍቃድ ሳይሆን ከላይ የታዘዘለት መሆኑን ይሰብክ ነበር። ይህ ዘውዳዊ የመንግስት ስርአት የስልጣን ምንጩ ህዝብ ሰላልነበረ የህዝብ ተጠያቂነት አልነበረበትም። ስልጣኑ በህዝብ የማይጠየቅ ከላይ የተሰጠ አይነኬ ነበር። ዘውዳዊው ስርአት በአጠቃላይ ለህዝበ የበላይነት መርህ እውቅና አልሰጠም።

ዘውዳዊው ስርአት የስልጣን ምንጩ መለኮታዊ በመሆኑ ራሱን እንደ ምሉዕ በኩለሄ ቢያስብም፣ ይህ አካሄድ በተለይ በ20ኛው ክፍለ ዘመን እየጎለበተ ከመጣው የዴሞክራሲ አመለካከት ጋር አልተጣጣመለትም። እናም ዴሞክራሲን ከተቀበሉ የአውሮፓ ሃገራት ጋር ሊመሰርተው የፈለገው ወዳጅነት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳርፍ በመረዳት፣ የንጉሰ ነገስቱን መለኮታዊ ስልጣን ምድራዊ ቅርጽ ለማስያዝ ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ሃይለስላሴ በ1923 ዓ/ም በቤተክህነት ሲተረጎም የነበረውን ፍትሃ ነገስት የተካ ህገመንግስት አጸደቁ። ይሁን እንጂ ህገመንግስቱ ንጉሰ ነገስቱ በሰየሟቸው ሰዎች የተዘጋጀ ነበር። ይህ ህገመንግስት የንጉሰ ነገስቱን ስልጣንና ክብር አይነኬነትና የዘር ሃረግ ተከትሎ የሚተላለፍ መሆኑን ይደነግጋል። የህግ አውጭው፣ የዳኝነት አካልና የጦር ሃይሉ በንጉሰ ነገስቱ የሚመራ ነበር። ህገመንግስቱ ሁለት ክፍል ያለው ፓርላማ እንደሚቋቋም ቢደነግግም፣ የላይኛው

ምክር ቤት አባላት በንጉሰነገስቱ የሚሰየሙ ሲሆኑ የታችኛው ምክር ቤት ደግሞ በመኳንንቱና በየአካባቢው ሹመኞች የሚሰየሙ ነበሩ። በዚህ ህገመንግስት ህዝብ ምንም ቦታ የለውም፤ የህዝብ የበላይነት አልተረጋገጠም።

ይህ ህገመንግስት በ1947 ዓ/ም ተሻሻለ። የተሻሻለው ህገመንግስት የንጉሱን ስልጣን ምሉዕ በኩለሄነት፣ ክብርና አይነኬነት የሚያጸና ነበር። በህገመንግስቱ መሰረት ሁለት ክፍል ያሉት ፓርላማ ተቋቁሟል፤ የህግ መወሰኛና የእንደራሴዎች ምክር ቤት። የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላትን፣ ሚኒስትሮችን፣ ዳኞችን፣ ከንቲባዎችን የመሰየም ስልጣን የንጉሰ ነገስቱ ነው። እርግጥ የእንደራሴዎች ምክር ቤት  አባላት በህዝብ የሚመረጡ ናቸው። የእንደራሴዎች ምክር ቤት አስፈጻሚው የሚያቀረበውን ህግ ያለመቀበል፣ የህግ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ፣ ሚኒስትሮችን የመጠየቅና የመመርመር ስልጣን ተሰጥቶታል። ይህ እንደአንድ ትልቅ መሻሻል የሚቆጠር ነው። ይሁን እንጂ የምክር ቤቱ አባል እጩ ሆኖ የመቅረብ መብት ያላቸው ቋሚ ሃብት ያላቸው ብቻ ነበሩ። በወቅቱ በነበረው ፊውዳላዊ ኢኮኖሚ ዋነኛው ቋሚ ሃብት መሬት በመሆኑ በእጩነት የመቅረብ መብት የነበራቸው ባለርስቶች ብቻ እንዲሆኑ አድርጓል። በወቀቱ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው መሬት አልባ ጭሰኛ አርሶ አደር ድምጹን የሚያሰማለት ወኪል የለውም። ከዚህ በተጨማሪ ከዘውዳዊው ስርአት የተለየ  የፈቀዱትን አመለካከት የመያዝ፣ በአመለካከት የመደራጀት፣ አመለካከትን የማራመድ፣ ሃሳብን የመግለጽ፣ የፕሬስ ነጻነት የመሳሰሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶች በህገመንግስት ስላልተረጋገጡ ምርጫው ዘውዳዊውን ስርአት የሚያጸኑትን ከመሰየም ያለፈ ምንም ፋይዳ አልነበረውም። ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ መብትና ነጻነት እንዳለው አካል (entity) ሳይሆን የነገስታቱ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ ተገዢ (subject) እነደሆነ ነበር የሚቆጠረው። ስርአቱ የህዝብ ውክልና ስላልነበረው የህዝቡን ጥቅምና ፍላጎት፣ መብትና ነጻነት የማስጠበቅ አቅምም ፍላጎትም አልነበረውም።

በመጨረሻ የህዝብ ውክልና ያልነበረውና የህዝብን የበላይነት ያልተቀበለው ዘውዳዊ መንግስት በህዝብ ትግል ተወገደ፤ መስከረም 2፣ 1967 ዓ/ም። ዘውዳዊው ስርአት በይፋ እንደተወገደ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች እርስ በርስ ተመራርጠው ያዋቀሩት ወታደራዊ ምክር ቤት (ደርግ) ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት መመስረቱን አወጀ። ወታደራዊው ደርግ የህዝብ ውክልና አልነበረውም። ወደስልጣን ሲመጣ ህገመንግስት አዘጋጅቶ ስልጣን ለህዝብ እንደሚያስረክብ ቃል ገብቶ የነበረ ቢሆንም ይህን ማሳካት አልቻለም።

ለአስራ ሶስት ዓመታት ያህል በጊዜያዊ መንግስትነት ስልጣን ይዞ የቆየውና የኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለም ተከታይ መሆኑን ያወጀው ወታደራዊው ደርግ ርዕዮተዓለማዊ የአመለካካት የበላይነት አለኝ የሚል እምነት ነበረው። በመሆኑም የአመለካካት ነጻነትን ማክበር አልፈቀደም። ወታደራዊው ደርግ ከሚከተለው የተለየ ማንኛውንም አመለካከት መያዝ፣ መገለጽ፣ በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር ተደራጅቶ ማራመድ የተከለከለ ነበር። ሃሳብን የመግለጽና የፕሬስ ነጻነትም በህግ የተገደበ ነበር።

ወታደራዊው ደርግ ከአስራ ሶስት ዓመት ቆይታ በኋላ ህገመንግስት አዘጋጀ፤ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት። ይህ ህገመንግስት የአመለካካት ነጻነት፣ ሃሳብን የመግለጽና የፕሬስ ነጻነት ባልተከበረበት ሁኔታ ህዝብን በቀጥታም ሆነ በውክልና ሳያሳትፍ የተዘጋጀ በመሆኑ የህዝብ ህገመንግስተ አልነበረም። የወታደራዊውን ደርግ ፍላጎት ብቻ መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነበር። በዚህ ህገመንግስት መሰረት የሃገሪቱ ገዢ፣ ወታደራዊው ደርግ ያቋቋመው የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ (ኢሰፓ) ብቻ ነው። ህገመንግስቱ  በመላ ሃገሪቱ በሚካሄድ ምርጫ የሚቋቋም ብሄራዊ ሸንጎ የተሰኘ የእንደራሴዎች ምክር ቤት እንደሚመሰረት ቢደነግግም፣ የምክር ቤቱ እጩወች በኢሰፓ ብቻ የሚወከሉ ስለነበሩ የተለያዩ

የህዝብ ፍላጎቶች የሚወከሉበት አልነበረም። ምርጫው በአንድ ፓርቲ በተወከሉ እጩዎች መሃከል ብቻ የሚደረግ፣ የተለያየ አመለካካት ያለውን ህዝብ ውክልና የማያረጋግጥ ነበር። በመሆኑም ወታደራዊው ደርግና ኢሰፓ የመሰረቱት መንግስት የህዝብ ውክልና አልነበረውም። እናም የህዝብ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች (የብሄር ብሄረሰብ እኩልነት፣ የግለሰብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች) ምላሽ ማግኘት አልቻሉም። ይህ ጭቆና የወለደው ህዝባዊ ትግል የዛሬ ሃያ ስድስት ዓመት ግንቦት 20፣ 1983 ዓ/ም የወታደራዊውን ደርግ ኢሰፓ መንግስት አስወገደ።

የደርግ መወገድን ተከትሎ ብሄሮችንና ብሄረሰቦችን በመወከል በትጥቅ ትግል ላይ የነበሩ ድርጅቶች እንዲሁም በሌሎች አመለካከት የተደራጁ ቡድኖች ያለምንም የአመለካካት ገደብ በአንድ አዳራሽ ታድመው በመመካከር የሽግግር መንግስት መሰረቱ። የሽግግር መንግስቱ የበላይ የስልጣን አካል የነበረው የተቃዋሚ ሃይሎች ምክር ቤት በህዝብ የተመረጠ ባይሆንም፣ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ ድርጅቶች በሚወክሉት ህዝብ እና የደርግን ስርአት ለማስወገድ በተካሄደው ትግል በነበራቸውን ድርሻ ልክ ስልጣን የተጋሩበት ስለነበረ የህዝብ ውክልና ባህሪ ነበረው። ይህ የሽግግር መንግስት፣ መንግስት ለመመስረት ያስቻለውን ህገመንግስት አዘጋጀ፤ የኢፌዴሪን ህገመንግስት።

የኢፌዴሪ ህገመንግስት አዘገጃጀት ሂደት ላይ ዝርዝር ጉዳዮችን አላነሳም፤ የቅርብ ጊዜ ታሪካችን በመሆኑ ብዙዎች ስለሚያውቁት። ይሁን እንጂ ህገመንስቱ መጨረሻ ላይ የጸደቀበት መንገድ ምሉዕ የህዝብ ተሳተፎን ስለሚያሳይ ልጠቅሰው እወዳለሁ። ህገመንግስቱ ህዝብ በተደጋጋሚ ተወያይቶበት ያዳበረው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ህገመንግስቱ የጸደቀው የህዝብ ውክልና ባለው ህገመንግስት አጽዳቂ ምክር ቤት ነበር። የህገመንግስት አጽዳቂ ምክር ቤት አባላት በህዝብ የተመረጡ ናቸው። ሁሉንም አመለካከቶች የሚወክሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ግልጽ፣ ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ ፉክክር በተሳተፉበት ምርጫ፣ ለአካለ መጠን የደረሱ ዜጎች በምስጢራዊ የድምጽ አሰጣጥ ስርአት መረጠው የወከሏቸው ነበሩ። በሃገሪቱ የህዝብ የስልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት የተረጋገጠበት የመጀመሪያው ሃገራዊ ምርጫ ይህ ነበር። የህዝብ ውክልና ባላቸው አባላት የተዋቀረው ምክር ቤት እያንዳንዱ የረቂቅ ህገመንግስቱ አንቀጽ ላይ ተወያይቶ በአብላጫ ድምጽ እያሳለፈ ነበር ህገመንግስቱን ያጸደቀው። በመሆኑም የኢፌዴሪ ህገመንግስት የህዝብ ህገመንግስት ነው። የኢፌዴሪ ህገመንግስት የህዝብ የበላይነት የተንጸባረቀበት ነው።

የኢፌዴሪ ህገመንግስት ብቸኛ የመንግስት የስልጣን ባለቤትና ምንጭ ህዝብ መሆኑን አረጋግጧል። በህገመንግስቱ መሰረት ከፍተኛው የመንግስት የስልጣን አካል በህዝብ የሚወከለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። ህገመንግስቱ የአመለካካት፣ የመደራጀት፣ ሃሳብን የመግለጽ፣ የመቃወም፣ የመምረጥና የመመረጥ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አረጋግጧል።

ህገመንግስቱ ስራ ላይ በዋለባቸው ያለፉ ሁለት አስርት ዓመታት አምስት ሃገራዊ ምርጫዎች እንዲሁም አራት አካባቢያዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በሚቀጥለው አመት አምስተኛ አካባቢያዊ ምርጫ ይካሄዳል። በእነዚህ ምርጫዎች ህገመንግስቱ ባረጋገጠው የፈቀዱትን አመለካካት የመያዝና የማራመድ፣ እንዲሁም የመደራጀት ነጻነት ተጠቅመው በሃገር አቀፍና በክልል ደረጃ ለመንቀሳቀስ የተመሰረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎቸ ያለአንዳች ክልከላ ተሳትፈውበታል። በምርጫዎቹ ላይ የተሳተፉ ፓርቲዎች በህዝብና በግል የመገናኛ ብዙሃን አማራጭ ፖሊሲያቸውን ለህዝብ አቅርበዋል። ህዝብ የፖሊሲ አማራጮችን በንጽጽር መመልከት እንዲችል በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃከል የፖሊሲ ክርክሮች ተካሂደዋል። በምርጫዎቹ ላይ የተሳተፉት የፖለቲካ ፓርቲዎች በመገናኛ ብዙሃን፣ በህዝባዊ ስብሰባ፣ በፖስተር፣ በጎዳና ላይ ትዕይንት ያለአንዳች ገደብ የምረጡኝ ቅስቀሳ አካሂደዋል።

መራጩ ህዝብም ያለአንዳች ተጽእኖ ለመራጭነት ተመዝግቦ ድምጹን የመስጠት መብቱ ተረጋግጧል። በኢትዮጵያ የተካሄዱት ምርጫዎች ላይ የተሳተፈው የድምጽ ሰጪ ህዝብ ብዛት የዳበረ ዴሞክራሲ ካላቸው ሃገራትም የተሻለ ነው። ይህ ወደስልጣን የመጣውን አካል የህዝብ ውክልና ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ አንዱ መለኪያ ነው። የህዝብ የበላይነት ማለትም ይህ ነው።

በሃገሪቱ ከተካሄዱ አምስት ምርጫዎች በተለይ እስከሶስተኛው ዙር በተካሄዱ ምርጫዎች የተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች የሃገሪቱ ከፍተኛው ይስልጣን አካል በሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ውስጥ መቀመጫዎችን የመጋራት እድል አግኝተዋል። በ3ኛው ዙር ይህ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር ይታወሳል። በተለይ የቀድሞው ቅንጅት በፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካገኛቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ መቀመጫዎች ባሻገር፣ አዲስ አበባ ከተማን ማስተዳደር የሚያስችለው ሙሉ የህዝብ ውክልና አግኝቶ ነበር። ይሁን እንጂ ቅንጅት *ሁሉን ማግኘት፣ ይህ ካልሆነ ሁሉን ማጣት* በሚል አካሄድ የተወሰነ የፌደራለ ምክር ቤት መቀመጫዎችንና አዲስ አበባን የማስተዳደር የህዝብ ውክልና ለመቀበል ፍቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ከዚህ ይልቅ የመረጠው ህዝብ በሃይል ስልጣን እንዲቀማለት በይፋ የአመጽ ጥሪ አስተላልፎ አዲስ አበባን ጨምሮ ደጋፊዎች በነበሩት አንዳንድ የሃገሪቱ ከተማዎች ውስጥ ሁከት ቀሰቀሰ። ይሁን እንጂ ሁከቱም ከሸፎ፤ ህዝብ የሰጠውም ስልጣን በተለይ አዲስ አበባን የማስተዳደር ስልጣንም አሻፈረኝ ብሎ ትልቅ የፖለቲካ ኪሳራ ላይ ወደቀ።

ይህ የቀድሞው ቅንጅት በፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስልጣን መጋራት፣ አዲስ አበባን ደግሞ ማስተዳደር የሚያስችል ውክልና እንዲያገኝ ያደረገ የግንቦት 7፣ 1997 ዓ/ም ሃገራዊ ምርጫ የግንቦት 20 ድል ፍሬ ነው። የበግንቦት 20 ድል ውጤት በሆነው የኢፌዴሪ ህገመንግስት የህዝብ የስልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት በመረጋገጡ የተገኘ ነው። ይህ የግንቦት 7፣ 1997 ዓ/ም ምርጫ የግንቦት 20 ፍሬ የሆነው የህዝብ የበላይነት የደረሰበትን ከፍታ የሚያሳይ ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል።

ይሁን እንጂ ከፍተኛ የህዝብ ውክልና አግኝቶ የነበረው የቀድሞው ቅንጅት የተከተለው ኢዴሞክራሲያዊ አካሄድ ዴሞክራሲውን ኮርኩሞት አልፏል። የቅንጅት ከሰላማዊ የስልጣን ውክልና ይልቅ የሃይል ስልጣን ምንተፋን መምረጥ፣ በተቃዋሚ ጎራ አለመተማመንን፣ መፈረካከስንና መዳከምን አስከትሏል። ይህም በመላ ሃገሪቱ በሚገኙ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተሰሚነት ያለው፣ ሃገር የመምራት አቅም ያለው ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ እንዳይኖር ከማድረግ በተጨማሪ ህዝብ በተቃዋሚዎች ላይ እምነት እንዲያጣ ምክንያት ሆኗል።

ይህ የተቃዋሚው ጎራ መኮሰስ፣ ኢህአዴግ ከጊዜ ወደጊዜ በአንጻራዊነት የተሻለ የህዝብን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ማርካት መቻል ጋር ተዳምሮ በአራተኛና አምስተኛው ዙር ሃገራዊ ምርጫ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በአብላጫ ድምጽ ሙሉ በሙሉ የምክር ቤት መቀመጫዎችን መቆጣጠር የቻሉበትን ሁኔታ ፈጥሯል። የገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ስኬትና ችግሮችን በራሱ ለማረም የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ በቀጣይ ምርጫዎችም የተለየ ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል ያመለክታሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ በቀላል አብላጫ ድምጽ ስርአት እየተሸነፉ ውክልና የሚያጡ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲኖሩ ምክንያት ሆኗል። መንግስት ይህን ችግር በመፍታት ሁሉም ድምጾች ውክልና ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ቃል ገብቶ ይህን እውን ለማድረግ በሃገር አቀፍ ደረጃ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ድርድር ማድረግ ጀምሯል።

እንግዲህ በኢፌዴሪ የመንግስት ስርአት ሃገር ህዝብ ነው። የመንግስት ስልጣን ባለቤትና ምንጭም ህዝብ ብቻ ነው። ይህ ባለፉ ሁለት አስርት ዓመታት በተካሄዱ ምርጫዎች ተረጋግጧል። ይህ ሃገርን ህዝብ ያደረገ፣ የህዝብን ብቸኛ የመንግስት የስልጣን

ባለቤትና ምንጭነት ያረጋገጠ የመንግስት ስርአት የግንቦት 20 ድል ውጤት ነው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በረካታ መቀመጫዎችን አሸንፈው ስልጣን የመጋራት እድል አግኝተውበት የነበረው 3ኛው ዙር የግንቦት 7 ምርጫ፣ እንዲሁም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመዳከማቸው ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶች የምክር ቤት መቀመጫዎችን ሙሉ በሙሉ ወደመያዝ የተሸጋገረበትን ሁኔታ በመቀየር፣ ሁሉም አመለካከቶች የሚወከሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር የተጀመረው እንቅስቃሴም የግንቦት 20 ድል ውጤቶች ናቸው።